# ዴሞክራሲያ

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (አንድነት) ልሳን *

ቅጽ 44 ቁ.3 ሐምሌ 2016

## ዛሬም ረሃብ በአገራችን

በኢትዮጵያ አገራችን በዘመነ ህወሓት የተከሰተውን ረሃብ አስመልክቶ ኢሕአፓ (አንድነት) ተደጋጋሚ መግለጫዎችንና ማሳሰቢያዎችን ማውጣቱ የሚታወስ ነው። ይህም ጉዳዩ ከባድ መሆኑን ታሳቢነት በማድረግና ዜጎች አስፈላጊውን ግንዛቤ በጉዳዩ እንዲያገኙና ግብረሰናይ ድርጅቶችም ለተጎጂው ወገናችን በወቅቱ እንዲደርሱ ለማሳሰብም ሲባል ጭምር ነው።

ዛሬም በተደጋጋሚ በሚያጠቃን የረሃብ ጉዳይ ላይ ትንሽ ማሳሰቢያ ማቅረብ አስፈልጓል። በረሃቡ የተጎዱት ወገኖቻችን የሚያስፈልጋቸውን የእህል፣ የጤንነት አገልግሎትና የንፁህ ውኃ አቅርቦት በተሟላ ሁኔታ እያገኙ አይደለም። ሕፃናት በረሃብ ዛሬም ይሞታሉ፤ እንስሳት ያልቃሉ፤ እስከ 20 ሚሊዮን የሚደርስ ረሃብተኛም በጠኔ ይንገላታል፤ በሞትና በሕይወት መካከልም ይናውዛል። ለሀገሪቱ ተተኪ የሆኑ ሕፃናት ከሞት ቢተርፉም በተሟላ ሥነ-አዕምሮና የአካል ጥንካሬ ውስጥ ሊሆኑ ስለማይችሉ የአምራችነት ኃይላቸው የቀነሰ እንደሚሆን የተመጣጠነ ምግብ እየተመገቡ ባደጉና የተመጣጠነ ምግብ አጥተው ባደጉት መካከል ያለው ሕይወት ምን እንደሚመስል በሙያው ላይ ጥናት ያደረጉ ባለሙያዎች ያስረዳሉ። ስለዚህ በአገራችን በረሃብ እየተገረፈ ያደገ ወጣት ለአገሩ እድገት የሚሰጠው ተስፋ እንዲቀንስ ያደርገዋል።

ታዲያ እነዚህን ረሃብተኞች ሊታደጋቸው የሚገባ ማነው? ተብሎ ቢጠየቅ መልሱ አስቸጋሪ አይደለም። "መቶ በመቶ ድምፅ ተመርጫለሁ" እያለ የሚወሸክተው መንግሥት ተብየው ነው። "የኢትዮጵያን ኤኮኖሚ በጥምር አኃዝ አሳድጌያለሁ" እያለ የሚፎክረው ራሱን ህወሓት/ኢህአዴግ እያለ የሚጠራው ኃላፊነት የጎደለው ቡድን ነው ተጠያቂው። ማጣፊያው ሲያጥርበትና በኢትዮጵያ ያለው ተጨባጭ ሁኔታ የህወሓት/ኢህአዴግን ፕሮፓጋንዳ አልገጥም ሲል ያው የፈረደበት የዓለም የአየር ጠባይ መለዋወጥና ኤል ኒኞ የተባለው የአየር ማዕበል ነውጥ በምክንያትነት ይቀርባሉ። እርግጥ ነው ከተፈጥሮ ጋር

ተያይዞ የሚመጣ ረሃብ በየትም ዓለም ይከሰታል፤ ነገር ግን ብዙ አገሮች ረሃብ ከመድረሱ በፊት አስቀድመው ዝግጅት በማድረግ ብዙ ጉዳት እንዳያደርስ አድረገዋል፤ ያደርጋሉም። እንደ ህወሓት/ኢህአዴግ ግን ዓይናቸውን በጨው ታጥበው ረሃብ የለብንም አይሉም። አገዛዙ የሌለውን ክብር ለመጠበቅ የማይሄድበት ርቀትና የማይቧጥጠው ቋጥኝ የለም። ሁሌም የሚያደርገው አንደኛው ዘዴው፣ ለናሙና የተዘጋጁ የአፈር ሽርሽራን ለማስወገድ፣ ዘመናዊ እርሻን ለማስተዋወቅና ትንንሽ ግድቦችን ለመሥራት የወጡ እቅዶችንና ሠርቶ ማሳያ ጣቢያዎችን የውጭ ጋዜጠኞችንና የግብረሰናይ ድርጅት አባሎችን በተጠና ስልት በመምረጥና በመጋበዝ እንዲሁም ወጪያቸውን በመሸፈን የጉብኝት ጉዞ ማዘጋጀት ነው። በዚህ ብልጣ ብልጥነት የተገዙ ወይም የተወናበዱ ጋዜጠኞችና ግብረሰናይ ድርጅቶች ከጉዞው በኋላ ጥሩ የድጋፍ ጽሑፎችንና ቪዲዮዎችን በመሥራት፣ "የኢትዮጵያ መንግሥት" ኢትዮጵያን ለማልማትና ረሃብን ታሪክ ለማድረግ" እያደረገና እየወሰደ ነው የሚሏቸውን እርምጃዎች ለዓለም ሕዝብ ያስተዋውቁለታል። ቃለ-አጋኖውንም በማጠናከር "ምንም እንኳን የዓለም አየር ፀባይ መለዋወጥ ከፍተኛ ተጽዕኖ ቢፈጥርበትም፣ የማይበገረው የኢትዮጵያ መንግሥት ..." እያሉ ማሞካሸት የተለመደ ድርጊታቸው ሆኗል።

ሁለተኛው ሌላው ዘዴ ደግሞ፣ የአገር ውስጥ ነፃ ጋዜጠኞችን ረሃቡ በተስፋፋባቸው የኢትዮጵያ ቦታዎች ጨርሶ ዝር እንዳይሉ ማገድና ስለረሃቡ ትንፍሽ እንዳይሉ ማዕቀብ መጣል ነው። ይህም ነፃ ኢትዮጵያውያን ጋዜጠኞችን እንደውጭ ጋዜጠኞች ማታለል ስለማይቻል፣ እንቅስቃሴያቸውን መገደብና የመጻፍ መብታቸውን መሸበብ ይሻላል ብሎ ያመነበት እኩይ ተግባር ነው። ይህንን ማዕቀብ አሻፈረኝ ብሎ ጥሶ፣ ዓባይ አካባቢ ያለውዴታቸው እየተፈናቀሉ ስላሉ ዜጎች በቅርቡ ለዘገባ የተንቀሳቀሰው ሙሉቀን ተስፋው የተባለ ኢትዮ-ምህዳር ጋዜጣ ባልደረባ ለእሥር መዳረጉ ማስረጃ ሲሆን የዓለምአቀፍ የጋዜጠኞች ማኅበር ይህ ሃቀኛ ኢትዮጵያዊ ጋዜጠኛ እንዲፈታ ጥረት እያደረገ ነው።

የፕሮፓጋንዳና የውሸት ጋጋታ በረሃብ ለሚሰቃየው ሕዝባችን ዳቦ ወይም የመጠጥ ውኃ አይሆኑትም። ረሃቡን ዓለም ካወቀውና ፀሐይ ከሞቀው ቆይቷል። አገዛዙ፣ “ድርቁ ወደ ረሃብ እንዳይለወጥ ከፍተኛ ጥረት እያደረግን ነው"፣ "በፊት በኢትዮጵያ ከታዩት ረሃቦች፣ ማለትም በንጉሡ ዘመንም ሆነ በደርግ ጊዜ ከነበረው ረሃብ ጋር ፈጽሞ የሚወዳደር አይደለም"፣ "በሺዎች ቀርቶ፣ በአሥሮች እንኳን ሰዎች አልሞቱብንም"፣ "የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ስትራተጂያዊ ዕቅዳችን ረሃብን ከኢትዮጵያ ምድር ለአንዴና ለሁልጊዜ አስወግዷል" እያለ ማደናቆርን ዋና ሥራው አድርጎ ተያይዞታል።

ያለንበት ዘመን መላው ዓለም በመገናኛ አውታሮች በቀላሉ የተገናኙበት ቢሆንም ምርቱን ከግርዱ፣ ውሸቱን ከእውነቱ ለማጣራት ትልቅ ጥረት ማድረግ የሚያስፈልግበት ወቅት ነው። ዕቃንና አገልግሎትን፣ ተፈላጊም ሆነ አልሆነ፣ ዋጋ ያለውም ሆነ አልሆነ፣ መሸጥ፣ መለወጥና ትርፍ ማግኘት ላይ የተዋቀረ ስልተ-ምርት ስለሆነ ያለው አረምና ግሳንግሱ እንደተፈላጊ ዕቃና ክብደት እንደሚያነሳ ንጥር ተቆጥሮ ሊሸመት የሚችልበት ዕድል አለ። ረሃቡን አስመልክቶ ግን የህወሓት/ኢህአዴግ ፕሮፓጋንዳ በውሸት የነቀዘ መሆኑ መታወቅ አለበት።

በህወሓት/ኢህአዴግ በኩል ይህን ግሳንግስና ግርድ ለመሸጥ በወር $50,000 የአሜሪካ ብር ከሚከፍላቸው የምዕራብ "የሕዝብ ግንኙነት አሻሻጮችና መልክ አሳማሪዎች" መካከል ዲ ኤል ኤ ፓይፐር (DLA Piper) የተባለ የዋሽንግተን ኮርፖሬሽን ይገኝበታል። ለአሻሻጮቹ የሚከፈለው ገንዘብ የኢትዮጵያ ሕዝብ አንጡራ ሀብት ነው። እንደ ኢትዮጵያ ያለች ረሃብተኛ፣ ተመጽዋችና ደሃ አገር ለሀብታም የምዕራብ ኮርፖሬሽን ይህን ያህል ገንዘብ በየወሩ መክፈል አሳዛኝና ዘግናኝ ተግባር ነው። እነዚህን ለመሳሰሉ ኩባንያዎች የሚከፈለው ገንዘብ የረሃብተኛ ወገናችንን ችግር ለመቅረፍ ስንትና ስንት ባገዘ ነበር። ብክነቱና ንቅዘቱ በዚህ ብቻ አይወሰንም። የተለያዩ ተአማኒነት ያላቸው ዓለምአቀፍ ድርጅቶች ደጋግመው እንደገለጹት፣ ባለፉት ዓመታት ከኢትዮጵያ 12 ቢሊዮን ዶላር ያህል በዝርፊያ ወደ ውጭ አገሮች እንደወጣና በውጭ ባንኮችና ሌሎች የገንዘብ ማሸሻ ሥፍራዎች እንደሚገኝ ተገልጿል። ይህም መጠነ-ሰፊ ገንዘብ በአጠቃላይ ከኢትዮጵያ ሕዝብ፣ በተለይም ከረሃብተኛው ሕዝብ አፍ ተነጥቆ የተወሰደ ገንዘብ ለመሆኑ አሌ አይባልም፤ ማንም የሚያውቀው ህወሓት በስርቆት ከአገር ያሸሸው የአገር አንጡራ ሀብት ነውና። ይህ የተዘረፈ ገንዘብ የአሁኑን ረሃብ ለማስወገድና ወደፊት ረሃብ በኢትዮጵያ ምድር እንዳይከሰት ለማድረግ ለሚረዱ ፕሮጀክቶች ማዋል ይቻል ነበር። $12 ቢሊዮን በር ከረሃብተኛ ላይ ዘርፎ የአሸሸ ጉዳኛውና ሀፍረተ-ቢሱ ህወሓት/ኢህአዴግ ይኸውና ዛሬ የልመና ኮረጆውን ይዞ "ረሃቡን ለማስወገድ $1.4 ቢሊዮን ያስፈልገኛል፣ ስለማምላክ ብላችሁ የእርጥባን እጃችሁን ዘርጉልን" እያለ የዓለምን ሕዝብ በመማጸን ላይ ይገኛል።

በዘመነ ህወሓት/ኢህአዴግ ኢትዮጵያችን እንዲህ ዓይነት አሳዛኝ አገር ሆናለች። ረሃብ የተንሰራፋባት፣ ዜጋ ጋዜጠኞቿ ስለረሃቡ እንዳይዘግቡ የታገዱባት፣ የውጭ ጋዜጠኞች የውሸት ዘገባ እንዲያቀርቡ ተንኮል የሚሸረብባት፣ ባለሥልጣናት ያላትንና የሌላትን ሃብት በቁሟ የሚመዘብሩባትና የአምባገነን አገዛዝ መልክ አሳማሪ የውጭ ተቋሞች የአባትህ ቤት ሲዘረፍ አብረህ ዝረፍ የሚለውን አባባል ተግባራዊ አድርገው ከሞኝ ደጅ ሞፈር ይቆረጣልን የሚለውን የአበው ብሂል ተግባራዊ ያደረጉባት አገር ሆናለች።

ረሃቡን ለመከላከልና ለማስወገድ ትርጉም ያለው ሥራ ለመሥራት ባለመቻሉም ተደማማሪ ችግሮች አብረው መታየት ከጀመሩ ቆይተዋል። የ2008 ዓ.ም. የበልግ የዝናም ወራትን ተከትሎ የመጣው በብዙ አካባቢዎች የጎርፍ አደጋና የመሬት መንሸራተት አደጋዎች ሲሆኑ፣ በረሃብ ከተጠቃው በብዙ ሚሊዮን ከሚቆጠረው ወገናችን በተጨማሪ በጎርፍ የተፈናቀሉ ወገኖቻችን ቁጥርም እስከ ሚሊዮን እንደሚደርስ ተገምቷል። በእንቅርት ላይ ጀሮ ደግፍ ይሏል ይህ ነው።

በአምባገነኑ አገዛዝና የተገዙ አፈቀላጤዎቹ፣ ተፈጥሮን ምክንያት አድርገው እንደ ጲላጦስ ከደሙ ንፁህ ነን ብለው እጃቸውን ከዕዳው መታጠባቸው አዲስ ነገር አይደለም። ረሃብና ጎርፍን የመሳሰሉ አደጋዎች ግን የተፈጥሮ አደጋ ብቻ ሳይሆኑ የፖለቲካ አደጋዎችም ናቸው፣ ስለዚህም መፍትሄውም ፖለቲካ ነው።

ከዚህ በፊት እኛም ሌሎችም እንዳሉት፣ የዘመነ-ህወሓት የረሃብ ምክንያቶች ከመሬት ፖሊሲው፤ ከመሬት ዝርፊያውና ዜጎችን ከማፈናቀል ርምጃዎቹ ጋር በጥብቅ የተቆራኙ ናቸው። መሬት ለአራሹ ከዛሬ 40 ዓመት በፊት አብዮተኛው ትውልድ መስዋዕት የከፈለበት መፈክር ቢሆንም፣ ዛሬም መፍትሄ ያላገኘ ጩኸት ሆኖ አራሹ ገበሬ የያዛት መሬት ከትውልድ ትውልድ፣ ከቤተሰብ ቤተሰብ እያነሰችና እየጠበበች በመምጣቷ፤ ለዕለት ጉርሱና ለዓመት ልብስ ወጭ የማትሸፍን ሆናለች። ገሚሱም እየጣላት ከተማ ሲገባና በለማኝነትና በቀን ሠራተኛነት ሲንገላታ፣ ወጣቶች አገር ጥለው በመሰደዳቸው ዕጣቸው በየበርሃው የአውሬ እራት መሆንና በየውቅያኖሱ መስጠም ሆኗል። አገር ጥለው ያልተሰደዱ ወጣቶችም ሕይወታቸውን ለማሰንበት ሲሉ በኅብረተሰባችንና በባህላችን ባልተለመዱ አስነዋሪ ሥራዎች ላይ ተሰማርተው ይገኛሉ። በቀየው የቀረው ደግሞ ከነቤተሰቡ በረሃብ ሲቆላ የሚታይበት አሳዛኝ ሁኔታ ላይ ነው የሚገኘው። ይባስ ብሎም ሰፋፊና ለም መሬቱን የዘመኑ ሹም ገበሬውን እያፈናቀለ ለውጭ ባለሀብቶች በርካሽ እየቸበቸበ፣ ተፈናቃዩ ለሱም ለቤተሰቡም የሚላስና የሚቀመስ አጥቶ በረሃብ የሚሰቃይባትን ኢትዮጵያ ነው የምናየው። ይህ በተለይ በአዲስ አበባ አካባቢ፣ በደቡብ ኢትዮጵያና ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ በሰፊው እየተካሄደ ያለ ሽያጭና ዘረፋ ሕዝባዊ ቁጣን አስነስቶ እንደነበረ የምናስታውሰው ነው። አሁንም ዝርፊያውና ማፈናቀሉ አልፎ አልፎ በአስከፊ ሁኔታ እየተካሄደ ነው። ለዚህም በአዲስ አበባ ላፍቶ ሠፈር የሕዝብ መፈናቀል አንዱ መረጃ ነው።

አገዛዙ በፈጠረው የዘር ፖለቲካ ምክንያት በሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ፣ የማንነት ጥያቄን የአነሱ ሰዎች ለመቅጣት ሀብታቸውንና መሬታቸውን እየተነጠቁ አገዛዙ ለሚፈልጋቸው ታጣቂዎች እየሰጠ ሰው-ሠራሽ ረሃብ እንዲስፋፋ አስተዋጽኦ አድርጓል። ይህም ከዘር ማጽዳት ወንጀል ጋር የተያያዘ እስከፊ ኢ-ሰብዓዊ ድርጊትና ዘግናኝ ሙብት ረገጣ የሚታይባትን ኢትዮጵያን ከፊታችን ደቅኗል። የመሬትና የኤኮኖሚ ፖሊሲው የውጭ ምንዛሬ በማግኘትና ገንዘብ በማከማቸት ላይ ያተኮረ ስለሆነም፣ ለም መሬት ለአበባ ተክሎችና ለጫት ቅድሚያ በመሰጠቱ፣ ለምግብ ፍጆታ የሚውሉ የእህል ዓይነቶች ወደ ጎን የተገፉበት ኤኮኖሚ በመሆኑ ለረሃቡ ተጨማሪ ምክንያት ቢሆን ሊገርም አይገባም። የውጭ ሸያጭ በቡና ምርት ላይ በማተኮሩና የቡና ዋጋ በማሽቆልቆሉ ከባንኮች ብድር የወሰዱ ኢትዮጵያዊ ቡና አምራቾች ብድራቸውን ለባንኮች መክፈል አልቻሉም። ስለሆነም በጊዜያዊነትም ቢሆን ከጥቂት ወራት በፊት አገዛዙ ጣልቃ በመግባት ባንኮች ብድራቸውን እንዳይጠይቁ ማገጃ እስከ ማውጣት የተገደደበት ደረጃ ላይ ደርሷል።

በአጠቃላይ የወቅቱ ረሃብ አገሪቷ ካለባት የተወሳሰበ የፖለቲካ፣ የኤኮኖሚና ማኅበራዊ ችግሮች ተነጥሎ ብቻውን የቆመ ችግር እንዳልሆነ በቀላሉ እንገነዘባለን። ለእያንዳንዱ ችግር ነው ብለን ላመላከትነው ጉዳይ ሁሉ፣ ፖለቲካዊ ወይም ኤኮኖሚያዊ ወይም ማኅበራዊ መነሾዎች አሉት። ለምን ኢትዮጵያዊ ጋዜጠኞች ስለረሃቡ ጋዜጣዊ ሽፋን አያቀርቡም ላልነው፣ በዛሬይቱ ኢትዮጵያ የመጻፍና የመናገር ነፃነት አለመኖሩ ይጠቀሳል። ለምን ሕዝባችን እየተራበ ዲ ኤል ኤ ፓይፐር (DLA Piper) በርካታ ሚሊዮኖች ብር ይከፈለዋል ስንልም፣ ኢትዮጵያውያን የሚፈልጉትን መንግሥት በሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ መንገድ መምረጥ አለመቻላቸውን ያመለክተናል። ለምን አርሶአደሩ የግሉ የሆነ የሚያርሰው መሬት አያገኝም? የራሳችንን ሕዝብ የመመገብ አቅም ሳንገነባ የውጭ ባለሃብቶች ለምን መሬት በሊዝ ያገኛሉ? ብለን ብንጠይቅም፤ በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ተለዋጭ ፖሊሲ ያላቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች በሰላማዊ ፉክክርና ነፃ ምርጫ የሚወዳደሩበት ሥርዓት በሩ የተዘጋ ነው የሚል መልስ እናገኛለን።

ለዚህ ነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከረሃብ ለመላቀቅ እንዲችል መሬት ለአርሶአደሩ ይሁን በማለት የኢሕአፓ ትውልድ ከፍተኛ መስዋዕትነት የከፈለው። ዛሬም ኢሕአፓ (አንድነት) መሬት ለአርሶአደሩ ገበሬ መሆን አለበት በማለት በድርጅቱ ፕሮግራም ውስጥ ነድፎ እየታገለ ነው። ለአንድ ገበሬ አለኝታውና የሕይወቱ ዋልታ መሬቱ ነው። መሬቱ የራሱ መሆኑን ካረጋገጠ ከራሱ አልፎ ለሌላው ኅብረተሰብ የሚበቃ ምርት ማምረት ይችላል። በአሁኑ የመሬት ይዞታ አካሄድ ግን የአርሶአደሩ ኑሮ የጭሰኝነት በመሆኑ የአገዛዙ ዕዳ

ከፋይ በመሆኑ የሚችለውን በማድረግ ምርት አምርቶ ቤተሰቡን መቀለብ አልቻለም። አገዛዙ በአምባገነንነትና በማን አለብኝነት እስከቀጠለና ዴሞክራሲ አስተዳደር በኢትዮጵያ ምድር እስካልተመሠረተ ድረስ፣ ሥርዓቱ ከታች እስከላይ በሙስና ነቅዞ የአገር አስተዳድር በተበላሸበት አገር ረሃብ እያሰለሰ ሕዝባችንን መፍጀቱ አይቀሬ ነው። ስለዚህ አገራችንን ለመታደግና የተሻለ ቀን ለማምጣት በጎ የምንመኝ ሁሉ በአንድነት ቆመን ሥርዓቱን ለመለወጥ የሚከፈለውን መስዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁ መሆን አለብን። ኢ.ሕ.አ.ፓ (አንድነት) ዛሬም እንደ ሁልጊዜው ሁሉን አቀፍ ሀገራዊ አካል መመሥረት ብቸኛ መፍትሄ ነው ብሎ ያምናል፣ ለዚያም ይታገላል።

በዴሞክራሲያዊ አስተዳደር ረሃብን ከምድረ-ገፃችን ማጥፋት እንችላለን!